# ከሥራ አጥነት ለመዳን የሚረዱ ሀሳቦች

ከዶ/ር ግርማ ሉሉ

የተለያዩ የምጣኔ ሀብት መረጃዎችን ስናገናዝብ የካናዳ የምጣኔ ሀብት (Economy) እድገት እንቅስቃሴ በ2010 ዓም ከመጀመሪያው ሶስት ወራት በኋላ እየተሻሻለ እንደሚሄድ እናያለን ። ለምሳሌ በ2010 ዓም የካናዳ ብሔራዊ አጠቃላይ የምርት እድገት (GDP) መጠን በ2% እንደሚጨምር የካናዳ ብሔራዊ ባንክ በቅርብ ባወጣው መግለጫ አስታውቆአል ። ይህ ዕድገት የአውሮፓ አገሮችን እድገት መጠን በእጥፍ የሚበልጥ ሲሆን የአሜሪካንን የ2010 እድገት ደግሞ በግማሽ (1/2%)እንደሚበልጥ ተገልጾአል ። የካናዳ አጠቃላይ የኤኮኖሚ እድገት በ2011 ከ 3.8% እንደሚዘል ይጠበቃል ይህ ደግሞ ከሁሉም አገሮች ዕድገት የሚበልጥ ይሆናል ። ከዚህ በተጨማሪ ለኤኮኖሚ እንቅስቃሴ መዳከም አንዱ ምክንያት የሆነው የሸማቾች የሸመታ እምነት ማጣት (consumer confidence )ሲሆን ይህ መለኪያ (Index) ላለፉት ስድስት ወራት መልካም (positive ) ደረጃ ላይ እንዳለ ተረጋግጦአል ። ስለዚህ በአሁኑ ሰዓት የምንሰማው የተለያየ ተስፋ አስቆራጭ ዜና ብዙ ሊያስጨንቀን አይገባም ። በተለይም በአልበርታ ክፍለ ግዛት ውስጥ ያለን ሁሉ በአሁኑ ሰዓት ከየትኛውም የካናዳ ክፍለ ግዛት ከኤኮኖሚ መቀዝቀዝ ቶሎ በሚያገግም ሥፍራ እንዳለን ማመን አለብን ።

የወደፊት የምርት እንቅስቃሴና የንግድ ሁኔታ ተስፋ ሰጪ ቢሆንም አንድ የታመመ ሰው ሙሉ ጤንነቱ እስኪመለስ ድረስ ህመሙ ብዙ የጎዳውን የሰውነቱን ክፍል እስኪያበረታ ድረስ ጊዜ እንደሚያስፈልገው ሁሉ ካለፈው September 2008 አንስቶ በጣም እየተዳከመ የመጣውን የእዚህ አገር የምጣኔ ሀብት ገበያ ወደ ፈጠነ የምርትና የንግድ እንቅስቃሴ ላይ እስከሚደርስ ድረስ ጉዳቱ ለተወሰነ ጊዜ እንዳለ መቆየቱ አይቀርም ስለሆነም ከሥራ የሚባረሩ ሰራተኞች ቁጥር እየጨመረ መምጣቱና ሥራ ለማግኘትም አድካሚ ሆኖ መቀጠሉ አይቀርም ። አንድ ኩባንያ ወይም የኩባንያ ባለቤት ዋነኛ ዓላማ ትርፍ ማግኘት ነው ። ትርፍ ማግኘት የሚችለው ደግሞ ያመረተውን ምርት ወይም የሚያቀርበውን አገልግሎት በብዙ ተጠቃሚዎች ሲፈለግ ነው ። የሸማቾች በምርቱ ላይ ያላቸው እምነት ወይም ፍላጎት ሲደክም የሺያጩ መጠን ይቀንሳል ያ ደግሞ የኩባንያውን ገቢ ይቀንሳል ። የአሠሪው ገቢ ሲቀንስ ደግሞ ወጪውን መሸፈን ያቅተዋል ። ስለዚህ ከኪሳራ ለመዳን የወጪውን ወይም የሚያመርተውን ምርት መጠን ለመቀነስ ይገደዳል ። ለአንድ ኩባንያ ዋነኛ ወጪ ደግሞ ለሰው ኃይል የሚከፍለው ክፍያ ነው ። ስለሆነም በስራው ላይ ለመቆየት የሸማቹ የመግዛት ፍላጎት እስከሚመለስ ድረስ የተወሰኑ ሰራተኞችን ከሥራ ማባረር አማራጭ የማይገኝለት መፍትሔ ይሆናል ። ስለዚህ በከተማችን እንደምናየው በርካታ የዘይት ኩባኒያዎች ለዚህ ዓመት ለአዳዲስ ፕሮጀክቶች የመደቡትን $30 Billion የካናዳ ዶላር ወደ $10 billion ቀንሰዋል ። Suncor ና Petro Canada ደግሞ ወጪያቸውን ለመቀነስና የምርት ቀልጣፋነትን ለማሳደግ ሲሉ በመዋሃዳቸው ሳቢያ 1400 ሰራተኞችን ከሥራ አሰናብተዋል ፔትሮ ካናዳም ተውጦአል ማለት ነው ። በርካታ ከሀበሻ ምድር የመጣ ህዝብ የሚሰራበት የእንጨት ሥራ ኩባንያም ወጪውን ለመቀነስ ሥራውን ወደ አሜሪካ በማዛወሩ ሳብያ በ2010 መጀመሪያ ላይ 600 ሰራተኞችን ያሰናብታል ። ይህ በከተማችን በቅርቡ ጊዜያት ያየነው ከብዙ ጥቂቱ ሲሆን ፤ በአገር ዓቀፍ ደረጃ ደግሞ ባለፈው ወር የመንግስት ዘገባ እንዳረጋገጠው የሥራ አጦች ቁጥር ወደ 8% አድጎአል ይህ ማለት ከ100 ሰዎች መሀል ስምንት ሰዎች ያለሥራ ቤት ቁጭ ብለዋል ማለት ነው ። በክፍለ አገራችን አልበርታ ይህ የሥራ አጥ ቁጥር ትንሽ ዝቅ ይላል ። ባለፈው ወር መረጃ የሥራ አጥ ቁጥር ባልበርታ በአሁኑ ሰዓት 7.4% ደርሶአል ። በካልጋሪ ከተማ ደግሞ ከ100 ሰዎች መሀል ሰባት ሰዎች በአሁኑ ሰዓት ያለ ሥራ አሉ ። ይህ አሀዝ በከተማችን ላለፉት ዓመታት ከታየው የሥራ አጥ ቁጥር ጋር መጠን ጋር ቢነጻጸር እጅግ ከፍተኛው ነው ። በዚህ አስቸጋሪ ወቅት አሰሪውችና ባለንብረቶች ከንግዳቸው መውደቅና ከኪሳራው ለማምለጥ በማስተዋልና በጥንቃቄ በርካታ እርምጃዎችን ይወስዳሉ ። ተቀጣሪ የሆንን ሰራተኞችም በዕዚህ

ወቀት ከቀጣሪዎቻችን ጋር ያለንን ግንኙነት መመርመርና ሥራችንን በብልሃትና በጥንቃቄ ማከናወን ይጠበቅብናል ።

ከዚህ ቀጥሎ ማንኛውም ሰራተኛ ከሥራ አጥነት ለመዳን ሊያደርግ የሚገባውን ጥንቃቄና ጠቃሚ ሀሳቦች ብዬ የማስበውን እገልጻለሁ ።

1ኛ <u>በስራ ላይ ለለን ሰራተኞች፤ በስራችን ለመቆየት የሚረዱን ሀሳቦች</u>

በአሁኑ ሰዓት ሥራ ላይ ያሉ ሰራተኞች የስራ ቦታቸውን አስተማማኝ ለማድረግ ከፈለጉ የግድ በአሰሪዎቻቸው ዓይን ለኩባንያው ጠቃሚና አስፈላጊ ሠራተኞች መሆናቸውን በተግባር ማሳየት ይጠበቅባቸዋል ። የኩባንያው ዋና ትኩረት ትርፍ ለማግኘት ስለሆነ ፤አንድ ሰራተኛ ለሚገኘው ትርፍ የሥራ ውጤት (productivity) ብዙ ተሳትፎ እንደሌለው ከታወቀ ከስራ የመባረሩት መሀል አንዱ እሱጩ ይሆናል መለት ነው ። የኤኮኖሚ እንቅስቃሴ በደከመ ጊዜ በኩባኒያው ውስጥ በቂ ስራም ቢኖር አሰሪዎች አጋጣሚውን በመጠቀም የጥራት እርመጃ ያካሂዳሉ ማለትም ሰነፍና ለጋሚ የሆኑ ሰራተኞችን የሚያስወጡበትና ታማኝና ታታሪ የሆኑትን ብቻ የምያስቀሩበት አጋጣሚ ይሆንላቸዋል ። ሲያባርሩም ሰነፍ ስለሆንክ ነው ብለው ምክንያት በመስጠት ሳይሆን ኢኮኖሚው ስለተዳከመ ነው ይላሉ ። ስለዚህ ከጥራት እርምጃቸው ለመዳን የሚከተሉትን ጠቃሚ ምክሮች በስራ ላይ ማዋል ብልህነት ነው ።

ሀ/ ***በሥራ ላይ በሰዓቱ መገኘት***- በሥራ ቦታችን ላይ ሁሌ በሰዓት መገኘት ቢቻልም አስራ አምስት ደቂቃ ቀደም ብሎ መገኘት፣ ለስራችን የምንሰጠውን ክብረ ያሳያል። የሥራ ሰዓትን የማያከብር ሰራተኛ ልክ ከአሰሪው ኪስ ገንዘብ እንደሚሰርቅ ማሰብ አለበት። ከሥራ ለሚቀርና ለሚዘገይ ሰው አሰሪዎች የሚከፍሉት ደመወዝ ኪሳራ ያለበትና የባከነ ገንዘብ ይሆናል ። ስለሆነም ብዙ ጊዜ የሚያረፍዱና በተለያየ ምክንያት ከሥራ የሚቀሩ ሰራተኞች በማጥራት እርምጃ ጊዜ በመጀመሪያ የሚባረሩ ይሆናሉ ።

ለ/ ***ለሥራው የለንን ታማኝነት ማሳየት*** -አንዳዶቻችን የምንሰራወን ስራ ላንወድ እነችላለን ሆኖም ገንዘብ ወይም ደሞዝ የሚያመጣልን ሥራ መሆኑ ነው። ይህ የገቢያችን ዋነኛ ምንጭ የሆነን ስራ በታማኝነትና ኃላፊነትን ለመወጣት በመጣር ካልሰራን በስፍራው ላይ ሆነን ማደግና መሻሻልን ማሰብ አንችልም ።

የእግዚአብሔር ቃል ቲቶ ምዕ 2፥9-10 በግልፅ እንደሚያስረዳው "ባሮች ለጌቶቻችው በማንኛውም ነገር እንዲገዙ፣ ደስም እንዲያሰኙአቸው የአፀፋ ቃል እንዳይመልሱላቸው አስተምር ፤ አይስረቁ ይኸውም በሁሉም መንገድ የአዳኛችን የእግዚአብሔር ትምህርት ይወደድ ዘንድ ፍፁም ታማኝ መሆናቸውን ያስመስክሩ ዘንድ ነው" ይላል ።

አብረወን ከሚሰሩትና ከመያሰሩን ሰዎች ጋር በመግበበት በመስራት የጌታ እየሱስ ደቀመዝሙር መሆናችንን ማሳየት ይጠበቅበወናል: ጌታንም ለማያውቁ ሁሉ ወንጌልን ለማካፈል የምንችለው ታማኝ ሆነን በስራችን ለይ ስንገኝ ብቻ ነው ። በሥራ ቦታ ታማኝ ሳንሆን ፤ የስራን ጊዜ እየሰረቅንና እየዋሸን የእግዚአብሔር ሰው ነን ብንልና ስለ ውንጌልም ብንናገር የሚሰማን አናገኝም ። ለምሳሌ ከ እ/ር ቃል አንደምንማረው የዮሴፍን የህይወት ጉዞ ብንመለከት ከባርነት አንስቶት ትልቅ የአገር መሪ እንዲሆን የረዳውና የመራው እግዚአብሔር አምላክ ቢሆንም ፤ ዮሴፍም እንደ እግዚአብሔር ሰው በባርነት በነበረበት ዘመን አሳሪውን በታማኝነትና በታታሪነት ያገለግልም ስለነበረ ነው ። ስለዚህም ከሌሎች ባሪያዎች ሁሉ ዮሴፍ ታማኝ ስለሆነ ከተራ እስረኛነት ወደ የእስረኞች አለቃ ረዳትና ኃላፊ የሆነው ። እኛም በተሰጠን ትንሹ ሥራ ታማኝ ሳንሆንና ውጤት ሳናሳይ ወደ ለተሻለ ሥራ የሚያስበን ማንም አይኖርም ። በመ/ቤታችን ውስጥ ዕድገት ለማግኘትና ሥራችን አስተማማኝ እንዲሆን ኃላፊነት መወጣትና ታማኝ መሆን ይጠበቅብናል ።

***ሐ/ሰላማዊ ግንኙነት መፍጠር*** -

ሌላው ጠቃሚ ጉዳይ ከአሰሪዎቻችንና ከሥራ ባልደረቦቻችን ጋር ያለንን ግንኙነት ማሳመር ። የእግዚአብሔር ቃል ቢቻል ከሁሉም ጋር በሰላም እንድንኖር ነው የሚመክረን ። ከሰዎች ጋር እየተጣላንና እየተነጫነጭን የምንሰራው ስራ ዕድገት ያመጣልናል ብለን የምናስብ ከሆነ በጣም ተሳስተናል።

አንዳንድ ጊዜ ተፅዕኖ ደርሶብን ውስጣችን ቢያዘንም ብስጭታችንና ንዴታችንን በአደባባይ መግለጽ አደጋ ስላለው ልንጠነቀቅ ይገባናል ።

መ/ ተገቢ **የመግባባት ችሎታና ቋንቋ** (proper Communication)- ከአስሪዎችና ከሰራተኞች ጋር በደንብ መግባባት ። ለመግባባት ደግሞ ተገቢ የመግባቢያ ችሎታና ጥብበ ያስፈልጋል ። ምናልባት የእንግሊዘኛ ቋንቋ ችሎታችን ጠንካራ አለመሆን ካሰሪዎቻችን ጋር በደንብ እንዳንግባባ እንቅፋት ሆኖብን ከሆነ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ትምህርት ቤት ገብተን ወይም በግል መጽሐፍትን ተውሰን በማጥናት ለማሻሻል መጣር ይገባናል ። ችሎታውና ዕውቀቱ ኖሮንም አነጋገራችን ጥራዝ ነጠቅ ከሆነ ማንም እንግሊዘኛ ተናጋሪ ስለማይሰማን ንግግራችንን ለማዳበር የአገሪቱ ተውላጆችን ጓደኛ በማድረግ ከእነርሱ ጋር በመዋልና ብዙ በመነጋገር ንግግራችንን ልናስተካክል እንችላለን ። እርምጃ ለመውሰድ ፍርሀትን ከውስጣችን እናውጣ ። **ሌላው የመግባቢያ ችሎታ (Ethic) ግብረ ገብነት ማንኛውም አሰሪ ወይም የበላይ አለቃ ሲያናግረን በግብረገባዊ አነጋገር መልስ መስጠት አለብን አለቃው ሲናገር በጽሞና አድምጦ መልስ እንድትሰጥ ሲያዝህ ብቻ መልስ ስጥ ፤ ሳያዝህ ጣልቃ ገብተህ አትናገር ። ጣልቃ ገብተህ ስትናገር አደገኛ ነው ተብለህ ነጥብ ስለሚያዝብህ ተጠንቀቅ በምንም ዓይነት እንደዚህ ዓይነቱን ጣልቃ ገብነት ካናዳውያን አለቆች አይወዱትም ።**

ሠ/**የሚወደትን ሥራ ለማግኘት በሙያ መሰልጠን**-የምንሰራውን ሥራ የማንወደውና ከሚያሰሩንና ወይም አብረውን ከሚሰሩት ጋር መግባባት ካልቻልን ወዲያውኑ የተሻለ ስራ ማፈላለጉ ብልህነት ነው ። በተበላሸ ሁኔታ ውስጥ ሆነን ዝም ብለን መመላለስ ጉዳት አለው። አሰሪዎች ከቤታቸው ገፍተው እስኪያስወጡን ድረስ መጠበቁ አላስተዋይነት ነው ። ለነገሩማ ሰው ውጤታማ የሚሆነው የሚወደውን ሥራ ሲሰራ ነው ። የምናምነውና ልባችን ውስጥ ጌታ ያስቀመጠውን ነገር ስንሰራ ሙሉ ሰላምና ደስታ ብቻ ሳይሆን በስራችንና በአገልግሎታችን እጅግ ውጤታማ እንሆናለን ።

የምንወደው ሥራ ላይ ለመሰማራት ደግሞ ዋጋና መሰዋትነት ከፍሎ ሙያውን መማርና በሙያው መሰልጠን ያስፈልጋል ። ጌታ ያበረታው ሰው በረጅምና በአጭር ጊዜ ዕቅድ ውስጥ የሙያ ስልጠናን እንደ ዕቅድ ቢይዝ እጅግ ጠቃሚ ነው ።

2ኛ/<u>**በአሁኑ ሰዓት ከሥራ ለተባረሩት የሚጠቅሙ ሀሳቦች**</u> ።

ሀ/ ከሥራ መባረርን እንደትልቅ አደጋ በመቁጠር ተስፋ አለመቁረጥ እንዲያውም እግዚአብሔር ወደ አዲስ የተለየ የተሻለ ሥራ የከፈተልን መውጫ በር አርገን መመልከት ጠቃሚ ነው ።

ለ/ የሥራ አጥነትን አጋጣሚ በመጠቀም ወዲያውኑ የሙያ ትምህርት መጀመር በአሁኑ ጊዜ የካናዳ መንግስት ለአለፉት ዓመታት በበለጠ ለሙያ ስልጠና ፕሮግራሞች ብዙ ገንዘብ መድቦአል፤ ማንኛውም ሥራ አጥ ሰው ከሃያ ሳምንታት በላይ የሚሰጥ የሙሉ ቀን ትምህርት ከተከታተለ የገንዘብና የነፃ ምክር ድጋፍ ስለሚሰጥ አጋጣሚውን መጠቀሙ ብልህነት ነው ።

ሐ/ ሰዎች ከስራ በተቀነሱ ሰዓት የተትረፈረፈ ጊዜ ስላላቸው አንዳንዶች ያልተጠበቀ ልምድና የስንፍናን ባህሪ ይወርሳሉ ። ሰዎች ከስራ ሲባረሩ ሌላ ሥራ እስኪገኝ ወይም አዲስ ነገር እስኪጀመር ድረስ እያንዳንዱን ደቂቃና ሰዓት ጠቃሚ ነገር ላይ ማሳለፍ እጅግ ተገቢ ነው ። በሥራ በተቀነሱበት ጊዜ የሚከፈል ድጋፍ ከመንግሥት ይሰጣል ፤ መንግሥት የሚከፍለው ገንዘብ እንደጡረታ ለዘለዓለም የሚሰጥ አይደለም ፤ ሌላ አዲስ ነገር እስከሚገኝበት ጊዜ ድረስ ከ19 -50 ሳምንታት ብቻ የሚከፈልነው ።ይህ ደግሞ በአገልግሎት ዘመናችንና በከፈልነው የዋስትና መዋጫ መጠን ላይ ይወስናል ። በእንደዚህ ከስራ

የመለየት ጊዜ ልዩ ጥናቶችን በማድረግ ወይም በአካባቢያችን በበጎ ፈቃደኛነት ለተወሰኑ ሰዓታት ነፃ አገልግሎት ለህብረተሰቡ በመስጠት ብንጠቀምበት ብዙ አዳዲስ ልምዶችን እንድንቀስም ይረዳናል ። በተለይ የበጎ አድራጎት አገልግሎት በምንሰጥበት ጊዜ ከማናውቃቸው ከብዙ ሰዎች ጋር ያስተዋውቀናል ፤ አዲስ በርም ልከፈትልን ይችላል። በሌላ አንፃርም ወንጌልንም ለማድረስ ትልቅ መስክ ሊሆንልን ይችላል ። **ቤት ውስጥ ተቀምጦ ጊዜን ማሳለፍ ሱቁን ዘግቶ ትርፍ የሚፈልግን ነጋዴን ያስመስላል ።**

## ማሰታወሻ

**ዶ/ር ግርማ ሉሉ የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤ/ክርስቲያን አባልና በሙያቸው በ** Royal bank of Canada wealth management department senior relationship manager **ሲሆን በትርፍ ጊዜያቸው ከቤተክርስቲያናት ጋር በመተባበር ስለቤተሰብ፣ ስለልጆች አስተዳደግና ስለገንዘብ አያያዝ ትምህርቶችን ያስተምራል ። ስለ ዝርዝር አገልግሎቱ የኢትዮጵያ ወንላዊት ቤተክርስትያን በካልጋሪ ቢሮን ማነጋገር ይችላሉ።**